የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በ ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 58
ADDIS ABABA, 26th April, 2016

<u>ማውጫ</u>

**CONTENTS**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፮/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለአራት ከተሞች መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.........ገጽ ፰ሺ፱፻፶፰

Proclamation No. 936/2016

African Development Bank Loan Agreement for financing Four Towns Water Supply and Sanitation Improvement Program Ratification Proclamation……………………..…...…Page 8958

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፮/፪ሺ፰ ዓ.ም**

**<u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለአራት ከተሞች መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፸፮ ሚሊዮን ፩፻፲ ሺህ የአሜሪካን ዶላር (ሰባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አስር ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ እ.አ.አ. ፌብሩዋሪ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No. 936/2016**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT BANK</u>**

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopian and the African Development Bank stipulating that African Development Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 76, 110, 000 USD (seventy six million one hundred and ten thousand United States Dollars) for financing Four Towns Water Supply and Sanitation Improvement Program was singed in Addis Ababa on the 3rd day of February 2016;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on 5th day of April 2016;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአራት ከተሞች መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሳኒቴሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፮/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ፌብሩዋሪ ፫ ቀን ፪ሺ.፲፮ አዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2000130014882 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘው ፸፮ ሚሊዮን ፩፻፲ ሺህ የአሜሪካን ዶላር (ሰባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ አስር ሺህ አሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በሥራ ላይ እንዲወል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "African Development Bank Loan Agreement for financing Four Towns Water Supply and Sanitation Improvement Program Ratification Proclamation No. 936/2016''.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 2000130014882 signed in Addis Ababa on the 3rd day of February 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopian and the African Development Bank is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 76,110,000 USA (seventy six million one hundred and ten thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of April, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESEIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**